# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 64 ህዳር 16 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ‹‹አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት ጋር ሆድና ጀርባ ነው›› ተክሌ በቀለ



# ቆይታ

## < <አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት ጋር ሆድና ጀርባ ነው> > ተክሌ በቀለ

የዛሬው «የቆይታ» አምድ እንግዳችን ተክሌ በቀለ ናቸው፡፡ ተክሌ በቀለ በተቃውሞ ጎራ ፖለቲካ ውስጥ ዘለግ ያለ ዓመታት ያስቆጠሩ ፖለቲከኛ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም የኢዴፓ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የትግራይ ተወካይ ነበሩ፡፡ በቀድሞ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲም ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ሰርተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ናቸው፡፡ ሕወሓት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሌሊት በሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ የፈጸመውን አሳፋሪ ጥቃት በማስመልከት በትግራይ ክልል ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ አነጋግረናቸዋል፡፡ ቆይታችንን እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ የፌዴራል መንግሥት ሕግ የማስከበር ሥራ እየሰራ እንዳለ ገልጿል ፡፡ በዚህ መልኩ ሕወሓት ግጭት ታስነሳለች ብለው አስበው ያውቃሉ?*

ሕወሓት ሰጥቶ የመቀበል ባህሪ ስለሌለው ያለፈው ታሪኩም ያንን ስለማይፈቅድለት ችግሩ በድርድር ይፈታል ብለን ባናምንም፣ እንደ ፓርቲም እንደ ግለሰብም ወደዚህ ችግር እንዳይገባ፣ ችግሮች በድርድር እንዲፈቱ በተደጋጋሚ ስንወተውት ነበር፡፡ ሕወሓት ግጭት ሊጀምር እንደሚችል፣ እርግጠኛ ብንሆንም በዚህ መንገድ ይጀምረዋል የሚል ግምት ግን አልነበረኝም፡፡

*በሰሜን እዝና በሕወሓት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ይገልጹታል?*

የሰሜን ዕዝ ማለት በኢኮኖሚም በማኅበራዊ ሕይወትም ለትግራይ ሕዝብ ዋስትናው ነው ፡፡ አመሠራረቱ ራሱ የአጭር ጊዜ ሳይሆን የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለው አመሠራረት ነው ፡፡ አመሠራረቱም ከኢትዮ - ኤርትራ ግጭት ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ከኤርትራ ጋር የነበረውን ግጭት እነሱ እንደ ጀመሩት በግሌ ባምንም፣ ታሪካቸው እንደሚመሰክረው ታሪካዊ የሆነ የምቀኝነት ባህሪ አላቸው፡፡ እነሱ ተመሪ የመሆን ፍላጎት የላቸውም፡፡ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ብትመጣ እኛ የበታች እንሆናለን የሚል አመለካከት ነበራቸው፡፡ አንዳንድ አመራሮችም እያንጸባረቁት ነው፡፡ የኤርትራና የትግራይ ሕዝብ በጣም እንዲራራቅ ይፈለጉ ነበር፡፡ ስለዚህ ያንን ግጭት ያመጡት እነሱ (ሕወሓቶች) ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ ከዛ ግጭት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጎን ነው የተሰለፈው፤ ህይወቱንም ለመስጠት ወደ ሰሜን ተጉዟል፡፡ በዛ ጥንስስ የሰሜን ዕዝ ተመሠረተ፡፡ ሰሜን ዕዝ ከሕዝብ ፍቅር ተነስቶ የተመሠረተ ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ለሰሜን እዝ ያልከፈለው መስዋዕትነት የለም፡፡ ከዛም በተጨማሪ ለ20 ዓመት ከሕዝቡ ጋር ማኅበራዊ መስተጋብር ፈጥሯል፡፡

*«ሕወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ናቸው» በሌላ በኩል ደግሞ «አይደሉም!» የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እርስዎ በትግራይ ስለነበሩ የትግራይ ሕዝብን ሥነ ልቦና በተሻለ ስለሚረዱ በዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢያጋሩን?*

የትግራይ ሕዝብን እና ሕወሓትን አንድ የማድረግ የረጅም ጊዜ ፕሮፖጋንዳ ስለተሰራ የሁለቱ ግንኙነት አንድ ሊመስለን ይችላል፡፡ ሕወሓት አንድ ሚሊየን አባላት፣ 300,000 ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አሉኝ ይላል፡፡ ግዙፍ የሆነ ትእምትን (ኤፈርትን) የሚያክል ኢኮኖሚ አለው፡፡ በርካታ ሠራተኞች በዛ ሥር ናቸው፡፡ ይሄን ሁሉ ስታየው እስከ ቤት ድረስ ሕወሓት ሊገባ ይችላል፡፡ ሚዲያ፣ ገንዘብ፣ መዋቅሩን በመጠቀም ሕወሓት ሙሉ ለሙሉ የትግራይን ሕዝብ ይዞታል ብሎ ቢያስብ ተሳስቷል ልትለው አትችልም፡፡ እውነታው ግን ያ አይደለም፡፡ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት ጋር ሆድና ጀርባ ነው፡፡ በትግራይ ሕዝብ ላይም በተደጋጋሚ ጊዜ ክህደት ፈጽሟል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ ከትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ውጪ ነው የጸደቀው፡፡ ከትግራይ ሕዝብ ጋርም ያኔ ነው መራራቅ የጀመረው፡፡ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሲጀመርና ሁለቱ ሕዝቦች ሲቆራረጡ ሕዝቡ የሕወሓት ስህተት መሆኑን አውቋል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ፣ ከኢትዮ ኤርትራ ጋር ጦርነት ሲገባ ሕዝቡና ሕወሓት ሆድና ጀርባ ሆኗል፡፡ በትግራይ ምድር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ላለፉት 27 ዓመታት የፓርቲና የመንግሥት መዋቅር አንድ ነው የነበረው፡፡ ይሄን ካስተዋልን የትግራይ ሕዝብና ሕወሓት አንድ አይደሉም ማለት እንችላለን፡፡

*ሕገ መንግሥቱን በማርቀቅ ሂደቱ ላይ የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ምን ነበር?*

ሕገ መንግሥቱ ከመፅደቁ በፊት በተደረገው ውይይት ላይ በወጣትነት እድሜዬ ተሳትፌበታለሁ፡፡ የትግራይ ሕዝብ «መሬት የእኛ የግላችን ይሁን!» የሚል መከራከሪያ አቅርቦ ነበር፡፡ ሌላኛው ሲያነሳው የነበረው ጥያቄም «ልጆቻችን አዲስ አበባ ሄደው ያስተዳድራሉ ወይስ አያስተዳድሩም?» የሚል ነበር፡፡ ልጆቻችን ሀገር የሚያስተዳድሩ ከሆነ አማርኛ ነው መማር ያለባቸው፤ አማርኛ የሥራ ቋንቋ መሆን አለበት እያለ ሕዝብ ሲከራከር ሰምቻለሁ፡፡ ሕወሃት ግን በስብሰባ 78 ቀናትን ከፈጀ በኃላ፣ ሰውን አደንዝዞ፣ ተሰላችቶ እንዲሄድ በማድረግ የራሱን ሃሳብ አፅድቆ ነው የሄደው፤ ይሄንን በአይኔ አይቻለሁ፡፡

የሕዝብ እንደራሴዎችም በፓርላማ ውስጥ አልነበሩም፡፡ በፓርላማ የነበሩት ሕወሓት ራሱ መርጦ ያመጣቸው ሰዎች እንጂ ሕዝብ የወከላቸው አልነበሩም፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማን እንደሚወረር እናውቃለን፡፡

*የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረ ፅዮን ቢሆኑም በተደጋጋሚ ከንግግራቸው እንደምንሰማው ከተግባራቸው እንደምንረዳው ጫና ያለባቸው ይመስላል፡፡ በእርስዎ ግምት ክልሉን ማን ነው እየመራው ያለው?*

ብዙዎች የሕወሓት ሰዎች እንደሚጽፉትና እንደሚናገሩት እንዲሁም የድርጅቱን ባህሪን ስናጤነው ከምስረታው ጀምሮ ከጀርባው ሌላ ኃይል አለ፡፡ እነዚህ ኃይሎች ከፓርቲው አመራሮች ጋር በጋብቻ፣ በአምቻ እና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በሕወሓት የሚወሰኑትና የሚተገበሩት ከመጋረጃ ጀርባ ነው፡፡ ከፓርቲው ጀርባ ከተብላላና ከተወሰነ በኋላ ነው ለውሳኔ ወደ ፓርቲው የሚቀርበው፡፡ በርካታ ጉዳዮችንም ከጀርባ ነው የሚጨርሱት፡፡ በአመራር ደረጃም ቢሆን ጥቂት ሰዎች ነው ተነጋግረው ውሳኔ የሚያሳልፉት፡፡ ለአብነት ያህል የኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ ብንመለከት ቁጥራቸው ከአምስት ግፋ ቢል ከስድስት የማይበልጡ የፖሊቲ ቢሮ አባላት ናቸው መጀመሪያ ሲነጋገሩበት የነበረው፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው ሳይሰማ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ብቻ ነው ሲነጋገርበት የነበረው፡፡ ውይይቱ ኢሕአዴግን አላካተተም ነበር፡፡ የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴም ከሕዝቡ እኩል ነው የሰማው፡፡ ሕወሓቶች፣ ኢሕአዴግ ላይ የሚሰሩትን ሥራ ሕውሓቶች ላይ ደግሞ በጀርባ የሚሰሩ ጥቂት ቡድኖች አሉ፡፡ በቤተሰብ የማሳመን ሥራ ከተሰራ፣ ወጣቶች ከተነሳሱ በኋላ ነው ለትግራይ ምክር ቤት ጉዳዩም የቀረበው፡፡ ይሄ የቆየ የድርጅቱ ባህሪ ነው፡፡ ከለውጡ በኋላ አኩርፈው የሄዱ ጀነራሎች፣ የደኅንነት ሰዎችና የደለቡ ነጋዴዎች ናቸው የትግራይ ሕዝብ እጣ ፋንታ ምን መሆን አለበት? እያሉ ሲነጋገሩና ተፅዕኖ ሲፈጥሩ የነበሩት

*አንዳንድ ሰዎች የፌደራል መንግሥት የሚወሰደውን እርምጃ በመቃወም አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ለሕወሓት ስልታዊ ድጋፍ እየሰጡ ይገኛል፡፡ ከምን የመነጨ ነው?*

አንዳንድ ሰዎች ሳይሆኑ አመለካካቶች ናቸው፡፡ ሁላችንም አንድ ዘር ነን፡፡ ቢያንስ ጥቁር አፍሪካውያን ነን፡፡ እነዚህ ሰዎች ከበረሃ ጀምሮ ሲመጡ «አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ» የምትል ሽፋን አለቻቸው፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የሚባል አስተሳሰብ በተግባር ያለ አይመስለኝም፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የሚባል አስተሳሰብ ቢኖር ኖሮ ብልፅግና በቀላሉ ሊፈጠር አይችልም፡፡ አብዮታዊነት ማለት ደግሞ ዓለም አቀፋዊነት ነው፡፡ የኩባ አብዮት እና የቻይና አብዮት ይደጋገፉ ነበር፡፡ ይሄ መደጋገፍ የአብዮታውያን መለኪያ ነው፡፡ እኛ ሀገር ውስጥ ሽፋን ናት፡፡ የእኛ ሀገሩ አብዮት ሕወሓት የቆመበት በቋንቋ ላይ የተመሠረተ በዘር ላይ የተመሠረተ ልዩነትን መፍጠር ነው፡፡ ስለዚህ ይሄ ፍላጎት ያላቸው የሕወሓት ሰዎች ብቻ አይደሉም፡፡ በአመለካከት ደረጃ ከየብሔረሰቡ መጣን የሚሉ እና ሕወሓትን መቃወም ቢፈልጉ እንኳን በዚህ መሠረት ላይ መቆም ይፈልጋሉ፡፡ በቋንቋ ላይ ልዩነቱን ፈጥሮ በዛ ላይ ገዢ መደብ ፈጥሮ ብሔረሰባቸው ማስተዳደር የሚፈልጉ ኃይሎች አሉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች አንዳንዶቹ አውቀውት አንዳንዶቹ ሳያውቁት የሚያደርጉት ያን መሠረት ለማስቀጠል ነው ፡፡


# አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)



ህዳር 16 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ወጣቱ የሚፈልገው የራሱን ፍላጎት ማሳካት ነው፡፡ ወጣቱ ሀገሩ የምትጠብቅበትን ሰጥቶ እሱም የሚፈልገውን ማግኘት ነው የሚፈልገው፡፡ ከዓለም ጋር ነው ውድድሩ፡፡ ይሄን የወጣቱን አመለካከት መምታት ይፈልጋሉ፡፡ ይሄ መርዝ መነቀሉ አይቀርም፡፡ ይሄ አስተሳሰብ ከተነቀለ ሕወሓትም ሆነ አንዳንድ ደጋፊዎቹ ህልውና የለንም ብለው ስለሚያስቡ ወደ ሥልጣን ለመምጣት ደግሞ ተወዳዳሪነትም ስለሚጠይቅ በቀላሉ እዚህ ውስጥ አንገባም ብለው ስለሚያስቡ፤ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ የሚያደርጉት ድጋፍ ነው፡፡

*በፊት ከምናውቃቸው ውጪ ሌሎች የትግራይ ተወላጆች ስለ ሕወሓት ክፋት እና ጨቋኝነት ወጥተው በአደባባይ ሲናገሩ አይሰማም ምክንያቱ ምንድን ነው?*

ሕወሓት የተለየ ሃሳብ የሚያራምዱ ሰዎችን በከፍተኛ ሁኔታ መታቸዋለች፡፡ በደርግም፣ በኢህአፓም፣ በኢዲዩም፣ በመኢሶንም... የነበሩ ኃይሎች በጣም ተመተዋል፡፡ እነዚህ እኮ ከእነሱ በላይ የነበረ ፓርቲን «አብረን እንስራ እንደራደር» ብለው እነዛም ፍቃደኞች ሆነው ተሃድሶ አድርገው አብረው ሲበሉ ሲጠጡ አምሽተው በሌሊት 9 ሰዓት እነዛን ረሽነው ሰፊውን የታጠቀው ወታደር፡- «ስትፈልግ ወደ ሱዳን፣ ብትፈልግ ሕወሓትን መቀላቀል፣ ብትፈልጉ ለደርግ እጃችሁን መስጠት ትችላላችሁ» ብለው የበተኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የትግራይ ምሑር ከፍተኛ ቅጣት ተቀጥቷል፡፡ በተለይ በዲያስፖራ በኩል ያሉት ዝም በማለታቸው በሚደርሰው በደል እና ጥፋት ከተወቃሽነት አያመልጡም፡፡ የእነሱ ዝምታ የትግራይን ሕዝብ ለዚህ አብቅቶታል ብዬ አስባለሁ፡፡

*መንግሥት «በሕወሓት ውስጥ የሚገኝ ቡድን» እያለ መግለጽ ጀምሯል፡፡ ይሄ ንግግር አንድምታው ምንድን ነው? ሕወሓትን መንግሥት በሽብርተኝነት ያልፈረጀበት ምክንያትስ ምን ሊሆን ይችላል?*

ሕወሓት ወደ አንድ ሚሊዮን አባላት ያሉት ፓርቲ ነው፡፡ አሁን የሚፈለጉት 96 የሚሆኑ አመራሮቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ነጥሎ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በትግራይ ውስጥ የሕወሓት አስተሳሰብ መነቀል አለበት፡፡ ይሄን አስተሳሰብ ለመንቀል በርካታ ሰዎችን አስረህ፣ ከሥራ አፈናቅለህ የሚሆን አይመስለኝም፡፡ መንግሥትም ሽኩሙን ማቃለሉ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በግሌ ምርጫ ቦርድ ምን እያደረገ እንዳለና ምን እየሰራ እንደሆነ ግራ ይገባኛል፡፡ ሕወሓት ከፌዴራል መንግሥት ውጪ የራሱን አወቃቀር ፈጥሮ ከሕገ መንግሥታዊ አካሄድ ውጪ በሆነ መልኩ ምርጫ አካሂዷል፡፡ በዚህ ድርጊቱ ከፖለቲካ ተሳትፎ መታገድ አለበት ብዬ አስባለሁ፡፡ ይሄን ማድረግ ያለበት ምርጫ ቦርድ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ የሕወሓት የፖለቲካ ተሳትፎ መታገድ አለበት፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶችን አሸባሪ ማለትን ግን በፊት ስናወግዘው የነበረ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሽብር ስጋት ይኖርባታል፡፡ ኢትዮጵያን ማሸበር የሚፈልጉ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ግን በሽብርተኝነት ፈርጀህ ፓርቲዎችን ማስቆም ጉዳት አለው፡፡ ከታች ጀምሮ አንድ የቀበሌም ይሁን የወረዳ አመራር ሽብርተኛ እያለ ሰዎችን የማሰቃየት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ሕወሓት አሸባሪ ቢባል በአካባቢው ተወላጆች ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል፡፡ እንዲታገድ እንጂ ድርጅቱ እንዲፈረጅ ፍላጎቱ የለኝም፡፡

*ሕወሓቶች ከራያና ከአላማጣ እስር ቤት የወሰዷቸው እንዲሁም ማረከናቸው ያሏቸው ሰዎች በህይወት ባይገኙ በአመራሮቹ ላይ ምን አይነት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል?*

በዚህ ኦፕሬሽን ውስጥ የሚሞቱም የሚያዙም አመራሮች ይኖራሉ፡፡ በሕግና በታሪክ ፊት ግን ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡ ራያ ላይ የተወሰዱት አስር ሺ ብቻ አይደለም፡፡ የራያ ሕዝብ በአስተሳሰቡም ሲለቀም ነው የነበረው፡፡ ወልቃይቶች በከፍተኛ ደረጃ ለርስታቸው ሲገደሉ ነው የኖሩት፡፡ ቁጥራቸው በእጅጉ ተመናምኗል፡፡ ሲያፍኗቸው፣ ሲያሳስድዷቸውና ሲያስገድሏቸው ነው የነበረው፡፡ ሕወሓት ሥነ ምግባር የሌለው ድርጅት ነው፡፡ አሁን ይዘዋቸው የሄዱት እንደራደርባቸዋለን ብለው ያሰቧቸውን ወጣቶች ይሆናል፡፡ መንግሥት ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ መቀሌ አካባቢ ኦፕሬሽኑ የተለየ መሆን አለበት፡፡ ይዟቸው የሄዷቸውን እስረኞች ምን ሊያደርጋቸው ነው የሚለውን ለወደፊት የምናየው ጉዳይ ነው፡፡

*መከላከያ ሠራዊት እየወሰደው ያለው ሕግ የማስከበር እርምጃ በቶሎ እንዲጠናቀቅ ምን ሊደረግ ይገባል?*

መንግሥት ይሄን ኦፕሬሽን ማሳጠር ይኖርበታል፡፡ ማኅበራዊ ቀውስ ጨምሮ የተለያዩ ችግሮች ይፈጠሩበታል፡፡ ነጻ የሆኑ አካባቢዎች ላይ ቶሎ አደረጃጀት መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ ዓለም አቀፋዊም ሆነ ሀገራዊ የበጎ አድራጎት ተቋማት ቶሎ ገብተው ማኅበራዊ ቀውስ እንዳይከሰት መሥራት አለባቸው፡፡ የፖለቲካ ሥራ መስራት መቻል አለበት፡፡ የትግራይ ሕዝብ ለአደረጃጀት አዲስ አይደለም፡፡ መልሶ ራሱን በራሱ ማስተዳደር ችሎ ለረዥም ጊዜ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ የፈረሰውን አደረጃጀት በአፋጣኝ አዲስ አደረጃጀት በመፍጠር ማደራጀት ይጠበቅበታል፡፡ የሚከፈለው ዋጋ ተከፍሎ ኦፕሬሽኑ የተሳካና በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ መሆን አለበት፡፡

*በወልቃይት እና በራያ ላይ ያለው ጉዳይ ቀጣይ የውጥረት አቅጣጫ እንዳይሆን ሥጋት አለ፡፡ መንግሥት ሊያደርገው የሚገባው ነገር ምንድን ነው?*

አሁን ለጊዜው ሕግ የማስከበር ሥራ ነው እየተሰራ ያለው፡፡ የሕወሓት አመራር ወንጀለኛ ነው፡፡ የሕወሓት አስተሳሰብ የኢትዮጵያ በሽታ ነው፡፡ እሱን አስተሳሰብ ለመንቀል ኦፕሬሽኑ የመጀመሪያ ግቡ መሆን ያለበት ሕወሓትን በመንቀል ላይ ነው፡፡

እነዚህ አካባቢዎች በሕወሓት በተያዙበት ጊዜ ከፍተኛ ሰቆቃ ተፈፅሟል፡፡ በተለይ ወልቃይቶች በቁጥር እንዲመናመኑ ተደርጓል፡፡ አሁንም በቡድኖች መካከል ጉዳት እንዳይከተል ከፌዴራል መንግሥቱ ልዩ ጥበቃ ለእነዚህ ያስፈልጋል፡፡ ከዛ በተረፈ ግን የትግራይና የአማራ ሕዝብ ነጻ መሆንና መወሰን ከቻለ እንኳን ይሄን ሌላ ትልቅ ችግር መፍታት ይችላል፡፡ ስለዚህ ሰከን ብሎ ሕዝቡ የሚነጋገርበትን የሀገር ሽማግሌዎች የሚወያዩበትን መድረክ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

የሰሜን ሰው ርስቱን እንዲሁም እያንዳንዱ ቀበሌ የማን እንደሆነ ለይቶ ያውቃል፡፡ ችግሩ እንዳይፈታ ሕወሓት አድርጓል፡፡ መንግሥት እነዚህን ሕዝቦች መጠበቅ አለበት፡፡ ትናንት ወልቃይቶችን ሲያሳድዳቸው ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ሌላውን ማሳደድ እንዳይኖር በዜጎች መካከል ግጭት እንዳይኖር ጥበቃ መደረግ አለበት፡፡ የሕወሓትን ሚና እተካለሁ የሚል ቡድን ከመጣ ደግሞ ጸረ ሰላም ነው ሊሆን የሚችለው፡፡

*ሕግ የማስከበር ሥራ ሲጠናቀቅ ምን አይነት ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል?*

ሕዝቡ መድኃኒት አጥቷል፡፡ የሚበላውም አጥቷል፡፡ ትግራይ ውስጥ በምግብ ዋስትና የሚኖር አንድ ሚሊዮን ገደማ ሕዝብ አለ፡፡ በርካታ ሕዝብም የዕለት ሥራ እየሰራ የዕለት ጉርሱን የሚሸፍን ነው፡፡ ሕዝቡ ስቃይ ላይ ነው ያለው፤ እንደ ቀይ መስቀል አይነት ተቋማት የዕለት ጉርስ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡ ከዛ ቀጥሎ ግን ነጻ የሆኑ አካባቢዎች ላይ ቶሎ ቶሎ መንግሥታዊ መዋቅር መደራጀት አለበት፡፡ መንግሥት እንደሚለው የወረዳና የቀበሌ አመራሮች ባሉበት ይቀጥላሉ የሚለውን አልቀበልም፡፡ ሕዝቡ እንደ አዲስ ማደራጀት ይችላል፡፡ የሚደራጀው አደረጃጀት ገለልተኛ የሆነ አደረጃጀት መሆን አለበት፡፡ ሕወሓትን የሚተካ የአንድ ቡድን አመለካከት ሳይሆን የትግራይ ሕዝብ ለቀጣዩ ምርጫ የሚያዘጋጅ የዴሞክራሲ ሥርዓትን የሚጥል መሆን አለበት፡፡ መከራ የደረሰበት አካባቢ ስለሆነ ከሌላው በተለየ መልኩ አርአያ የሚሆን አስተሳሰብ መጠቀም መቻል አለበት፡፡

*አሁን ከሚታየውና ከሚሰማው አንጻር የትግራይን ክልል በቀጣይ ሀገር አቀፍ ምርጫ ማሳተፍ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል?*

የትግራይ ሕዝብ ብዙ መከራ ያሳለፈ ሕዝብ ነው፡፡ ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያደርግ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ ፊውዳሎች እንበላቸው እንጂ አባቶቻችንን ሀገር አስተዳደር ሲያስተምሩት የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ መደራጀትን ባህሉ አድርጎ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ አሁንም ራሱን አደራጅቶ የመውጣት እድል ይኖረዋል፡፡ ብዙ ጊዜም አይፈጅበትም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥትም ባለቸው አቅም የትግራይን ሕዝብ ያግዙታል ብዬ አስባለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላታችን ሕወሓት ነው ብሎ ያስባል፡፡ እሱ ከጠፋ በቁጭት ከጎኑ ይሰለፋል፡፡ ይሄንንም ፈተና ያልፈዋል፡፡

*ኢዜማ፣ የፌዴራል መንግሥት እየወሰደ ለሚገኘው ሕግ የማስከበር እርምጃ ድጋፉን ገልጿል፡፡ በቀጣይ ሕዝቡን ከማረጋጋት አንጻር እና ወደ ቀድሞ ህይወቱ እንዲመለስ ለማድረግ ምን ሊሰራ አቅዷል?*

ኢዜማ መልሶ ማቋቋሙን የሚደግፈው ነው፡፡ ጊዜያዊ አስተዳዳሪዎች የሚባሉት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡ ኢዜማም ይሄን ጥሪ ተቀብሎታል፡፡ እዛ ውስጥ የሚሰሩ ሰዎችን መድቧል፡፡ አብዛኛው የትግራይ ተወላጆችና የሌሎችም አካባቢ ተወላጆች ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ንቁ ተሳትፎ እያደረገ ነው፡፡ እንደ ፓርቲ በሰብዓዊ እና በማኅበራዊ ጉዳዮችም ላይ ይሰራል፡፡ በፖለቲካም ንቁ ተሳታፊ በመሆን ፓርቲዎችን በማገዝና ተባብሮ በመሥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ የትግራይ ሕዝብ ችግር እንዲፈታ ንቁ ተሳታፊ ይሆናል፡፡

*በስተመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎትና ቃለምልልሳችንን እንቋጨው፡፡*

መልዕክቴን በትግርኛ ቋንቋ ነው ማስተላለፍ የምፈልገው፡፡

*ይቻላል፡፡*

እቲ ለለናሉ እዋን ናሕጊ ምኽባርን ምሕላው ልኣላውነትን እዩ። መርዚ ልኾነ ዘርኣውነትን ቁሽታዊነትን ነቂሊና እንቀብረሉ እዋን እዩ። በዚ ዘመቻ እዚ ኣጋንንቲ ዝኾኑ መራሕቲ ህወሓት ጥራኽ ለይኾነስ እሶም ብኣምሳሎም ልፈጠርዎም ካልኦት ኣጋንንቲ ፍጥረታት ብለዎም ኣቕሚ ኩሉ ምንቅስቃሶም ኣይተርፍን። ንዕዘበ ለለና ጉዳይ ኮይኑ ኣሎ። እዚ መርዚ እዚ ኣብ ትግራይ ይኹን ኣብ መላእ ሃገርና ክንቀል አለዎ። ስለ ልኾነ ድማ መላእ ህዝብና ፣ ናይ ምግባረ ሰናይ ውዳበታት ፣ ሚድያታት ሃገርና ፣ ፈተውቲ ህዝብን ሃገርን ዝኾና ፖለቲካዊ ውዳበታት ኣብ ጎኒ መከላኸሊ ሃገርና ጠጠው ክብላ ይግባእ። ነቲ ንኣስታት ፍርቂ ክፍለ ዘመን ኣብ ዝባን ህዝቢ ሰፊሩ ዝነበረ ኣጋንንቲ ቦቂስና ብምቅባር ኣብ መቃብሩ ትግራይ ሞዴል ናይ ልምዓት ፣ ሰላምን ዲሞክራስን ክትከውን ክንረባረብ ይግባእ። ነቲ ገጢሙና ዘሎ ኣብ ንቀጻልነት ለ ክገጥመና ዝኽል ሰብኣዊነትይ ጸገም ኢኮኖሚያዊን ብሓባር ክንምከቶ ይግባእ ይብል።

ከላይ በትግርኛ የተላለፈው መልዕክት ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

«ያለንበት ሁኔታ በተለይም በዚህ ሕግን የማስከበርና የህልውና ዘመቻ የዘረኝነትና የመንደርተኝነት መርዝ የሆነውን መንፈስ ነቅሎ የመቅበር ጉዳይ ነው። በዚህ ዘመቻ የሕወሓት አጋንንቶች ብቻ ሳይሆን ሌሎች የነሱ ፍጡራን የሆኑ አጋንንቶችም ባላቸው አቅም ሁሉ መንቀሳቀሳቸው አይቀርም። እያየን ያለነውም ይህንን ነው። በመሆኑም ሕዝብ፣ የሰብአዊና በጎ አድራጊ ተቋማት፣ ሚድያዎችና ሀገርን የሚያስቀድሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገጠመንን ችግር ለመፍታት እንደተጀመረው ከመከላከያችን ጎን ልንቆም ይገባል። ሁላችንም ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል የቆየው መርዙ እና አጋንንቱ ከተነቀለ በኋላ ትግራይ የልማት ፣ የሰላም እና የዲሞክራሲ ሞዴል እንድትሆን መረባረብ ይገባናል፡፡»

*ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡*

እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ፡- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!

# ፓለቲካ ለእኔ ትውልድ

## የትውልድ ክፍተት ሰለባው!

ሐብታሙ ኪታባ



የሰው ልጅ በትውልድ ቅብብሎሽ ጉዞ ውስጥ ነው:: አሳክቶ ማለፍ የፈለገውን ለማድረግ ሲል ያስኬደኛል ብሎ ባሰበው መንገድ ውስጥም ይጓዛል:: ጉዞውም በታሪክ ገጽ ላይ በሚጻፉ ድልም ሆነ ሽንፈት ሊገለጽ ይችላል:: መጪው ትውልድ ከታሪክ መዛግብት ጋር የሚያጠፋው ጊዜ ስሌቱ ቀጣዩን ጉዞ የተሻለ ማድረግ የሚቻልባቸው አቅጣጫዎችን ለመፈለግ በጥቅል የትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ትርፋማ መሆንን በማለም ነው:: የተፈጥሮ ሳይንሱም ሆነ ማኅበራዊ ሳይንሱ ውስጥ የተቀመረው እውቀት የሰው ልጅ በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ የተሻለውን ለማየት የሚያደርገው ጉዞ ማሳያ ነው ብንል የተሳሳትን አንሆንም:: ፖለቲካም መዳረሻው ይኸው የተሻለውን ለዜጎች ማድረሻውን መንገድ መተለም ሆኖ ተተርጉሟል::

ወ/ሮ አቢጌል እጅ የገባው ደብዳቤ ታሪክ ለመስራት የቆረጠ ትውልድ አካል የሆነውን የቁርጥ ሰዓት ሰውን መልዕክት ይዟል:: እርሷ ከጓዳዋ እርሱ ከትውልድ አባቶች ሸንጎ:: የአቢጌልን ደብዳቤን የከተቡት እጆች የደከሙላት ሀገር ዛሬም የምድራችን የፖለቲካ ስበት ሆና ቀጥላለች:: የተባበሩት መንግሥት ድርጅትን መቀመጫም ሆነ መንፈስ በጉያዋ አድርጋ በትረ ሥልጣንን ከአንዱ ወደ አንዱ እያደረገች ነው:: አሜሪካ!!! በትውልድ ቅብብሎሽ ከጠመንጃ ይልቅ በጠመኔ ፖለቲካ የምትመራ ሀገር፤ መናገሻ ዘ ሰው ልጆች!!!

ቅዳሜ ረፋድ አራት ኪሎ ዞሪያ ካሉ ካፌዎች የቅዳሜ ጋዜጦችን ይዘው በተመስጠ ያሉ በእድሜ የገፉ አባቶች አጠገብ ጠጋ ብለህ ጨዋታ ጀምር:: ቀስ ብለህ ጨዋታውን ከኢትዮጵያ ጋር ለማገናኘትም ሞክር:: ከእዚህ በኋላ እመነኝ ታላቅ የእውቀት በር ተከፈተልህ ማለት ነው:: የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የአዲስ አበባን ታሪካዊ ክስተቶች፣ የንጉሡን ሆነ የወታደሩን፣ የካራማራን ሆነ የሽራሮን፣ ስለ ኢትዮጵያ አቢጊሎች፣ በኪሳራ ሂሳባቸው ስለተዘጉ ዘመናት፣ ስለ መፍትሄው ሆነ ስለ ሌላውም ይተነትኑልሃል:: ትውውቅህ ዘልቆ "አባባ እርስዎ በምን አቅጣጫ ሀገርዎትን አገለገሉ?" ካልካቸው በሃሳብ ጭልጥ ብለው የወጡ የወረዱበትን አንስተው ያጫውቱሃል:: የወጡ የወረዱትን ከትላንት ጋር አገናኝተው ለነገው በማቀበል ረገድ ኃላፊነታቸውን እንደ ትውልድ ስለመወጣታቸው የሚያስቡትን ከጠየካቸው ቅጭም ብለው ከጥቁር የታሪክ መዝገባችን ስማቸው ከስርዓት በላይ ወደ ሆኑ ግለሰቦች ይጠቁሙህና የትውልድ ኪሳራውን በጣት በማይሞሉ ግለሰቦች ላይ አድርገው ጨዋታቸውን ይቀጥሉልሃል :: ጋዜጣ ማገላበጡን ትተህ በምናብህ ዶክመንተሪ በነጻ ትኮመኩማለህ:: እሁድ ማለዳም ከተመለስክ መሰል የታሪክ መዝገብን የሚገልጡ ያጋጥሙሃል:: ቤተመንግሥቱን በቅርብ እርቀት እያየሁ ወደ ፒያሳም ሆነ ካዛንችስ ልሻገር ብትልም በታሪክ የበለጸጉትን አታጣቸውም:: ኢትዮጵያ!!! በትውልድ ቅብብሎሽ ሉዓላዊነትን ማስከበር የቻለች ግን ከጠመንጃ ወደ ጠመኔ ለማምራት እያማጠች ጠመኔው በባለ ጠመንጃው እየተሰበረ የምትቸገር ሀገር፤ መናገሻ ዘ ብሄር!!!

### መዳረሻ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ያለው የትውልድ ክፍተትን ስፋት በምን እንደሚለካ እርግጠኛ ባልሆንም ሰፊ የሚለውን ቃል ልጠቀም:: በአጭር ጊዜ ውስጥ የመደፈን እድሉ አነስተኛ የሚመስል የትውልድ ክፍተት ባለባት ሀገር ውስጥ ፖለቲካ የሕጻናት እቃ እቃ ጨዋታ ቢመስል ሊገርመን አይገባም:: በእርግጥ የትውልድ ክፍተት ▶



▶ በፖለቲካ ብቻ የሚታይ ከመሰለን ስህተት ላይ እንወድቃለን:: አንድን ዘርፍ ለይቶ የሚያጠቃ የትውልድ ክፍተት የለም፤ እንደ

> «በአጭር ጊዜ ውስጥ የመደፈን እድሉ አነስተኛ የሚመስል የትውልድ ክፍተት ባለባት ሀገር ውስጥ ፖለቲካ የሕጻናት እቃ እቃ ጨዋታ ቢመስል ሊገርመን አይገባም:: በእርግጥ የትውልድ ክፍተት በፖለቲካ ብቻ የሚታይ ከመሰለን ስህተት ላይ እንወድቃለን:: አንድን ዘርፍ ለይቶ የሚያጠቃ የትውልድ ክፍተት የለም»

ኮቪድ 19 ሁሉንም አንድ በአንድ እንጂ:: የእዚህ ጽሁፍ መዳረሻ ግብ ይህን የሚያነበው በፖለቲካ ውስጥ ያለ ሰው በከፍተኛ የትውልድ ክፍተት ውስጥ ባለች ሀገር ውስጥ የሚጫወተው ሚና ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ማስገንዘብ ነው:: በተጨማሪም ወደ ፖለቲካ ለመቀላቀል ፈራ ተባ ለሚሉቱ የአንድ ተጨማሪ ሰው ፖለቲካዊ አስተዋጾ ትርጉሙ ትውልዳዊ መሆኑን ለማስረዳት ነው:: በወ/ሮ አቢጌል ተሞጋሽነት የምትታወቀው አሜሪካ ትራምፕን እያብጠለጠሉ "ስለ አሜሪካ ዲሞክራሲ ብለንዎታል" እያሉ የሚተቹትን በምናደምጥበት በእዚህ ወቅት "ስለ አሜሪካ ዲሞክራሲ" ስለሚለው መቅድም ጥቂት እንበል:: እኛም ትራምፕን በአሜሪካ ዲሞክራሲ ስም እንማጠንው፤ ደግሞም ተማጥነነዋል::

### ትራምፕን "በአሜሪካ ዲሞክራሲ"

ትውልዷን ተቀብላ እየሸኘች በተረጋጋ ፖለቲካ በትረ ሥልጣንን ከአንዱ ወደ አንዱ እያሻገረች አወዛጋቢውን ሰው ከነጩ ቤት ልታስወጣ ቀናትን እየቆጠረች ያለችው አሜሪካ የትውልድ ቅብብሎሽ ምሣሌነቷ ከፍ ያለ ነው:: በዲሞክራሲ አብነት የምትታወቀው ሀገር ከትራምፕ የምርጫውን ውጤት አልቀበልም በሚለው ጉዳዩን ወደ ሸንጎ ይዞ ለመሄድ ዶሴ ማሰናዳት ሂደት ውስጥ "ስለ አሜሪካ ዲሞክራሲ ሲሉ" ብለው ትራምፕን የሚመክሩ በርክተዋል:: የትራምፕ ቤተሰብ በትራምፕ አቋም የተነሳ በተለያየ አቋም ላይ መገኘቱን ተከትሎ ሁነቱን በስልጣኔ መነጽርም የሚመለከቱት አልጠፉም:: በአሜሪካ አየር ላይ እየሆነ ያለው ነገር ያላማራቸው የጠመንጃ ሸመታ ውስጥም ሰንብተዋል:: የጠመንጃ ሸመታው ከወትሮው የተለየ ነበር ሲባል አሜሪካ ወዴት የሚል ስጋት ፈጥሯል:: ስጋቱ መፈጠሩ አንድ ጉዳይ ሆኖ ስጋቱ በሚያሳድረው ሀገራዊ ተጽእኖ ላይ ግን ያለው አቋም ከአሜሪካ ተቋማት ጡንቻ ያለፈ ችግር ይፈጠራል ብሎ በልበሙሉነት ትንታኔን የሚያቀርብ ግን አልተሰማም::

የትራምፕ ተቺዎች "የአሜሪካ ዲሞክራሲ" በምትል መቅድም ውስጥ ተጠልለው እያብጠለጠሏቸው ቀጥለዋል:: የአሜሪካ ዲሞክራሲ የምትለው መቅድም የሚያስተላልፈው መልእክት የአሜሪካ ዲሞክራሲ በአርዓያነት የሚነሳ መሆኑን የሚገልጥ ነው:: እውነትነቱን አንባቢውም ጸሃፊውም በቀላሉ የሚስማሙበት ይመስላል:: ይህ ክስተት የተፈጠረው ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን የኢትዮጵያን ዲሞክራሲ ክብር አሳጡት የሚል ክስ ሊቀርብ ስለማይችልም ስምምነታችን ይዘልቃል:: አሜሪካኖቹ የቱንም ያህል ጠመንጃ ግዢ ውስጥ ቢሆኑ፤ ትራምፕ የቱንም ያህል ውጤቱን አልቀበልም ቢሉ የትራምፕ ውሳኔ አሜሪካንን እንደ ሀገር ከመቀጠል ስጋት ውስጥ የሚጨምር ወይንም እንደ እኛ ምርጫ 1997 ዓ.ም. በታሪክ ፊት አንገት የሚያስደፉ ገጾችን የሚጨምር አይመስልም:: ምክንያቱ ሆኖ የሚቀርበው በአሜሪካ የሚገኙት ጠንካራ ተቋማት እና የዜጎች ዲሞክራሲያዊ የአዕምሮ ውቅር ነው::

ይህንን አይተን ወደ ሀገራችን ስንመጣ የተለመደውን የተቋማት ግንባታ ውትወታ የዝማሬውን የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ራሳችንን እናገኛለን:: የመጀመሪያው ስንኝም የተቋም ፍላጎታችንን በሚገባ ይገልጻል:: በሁላችን ዘንድ በኢትዮጵያችን የተረጋጋ እድገት ውስጥ የተቋማት ግንባታን ለነገ የሚባል ሥራ እንዳልሆነ መናገራችን ሆነ መጻፋችን ትክክለኛነቱን አስረጂ አይፈልግም:: ይህ መጣጥፍ በመሻታችን እና በተጨባጭ ፍሬያችን መካከል ያለው ልዩነት ውስጥ አንድ ትኩረት ያልተሰጠው ከተቋማቶቹ ግንባታ ጀርባ ስለሚገኝ ቁልፍ ሃብት ያነሳል:: ከዘመናይ ቁሳቁስ ሆነ ከተቋማቱ ሰማይ ጠቀስ ህንጻ በፊት አንድ የተዘነጋም እንዲሁ በቀላሉም ወደ መሆን ለማምጣትም ጊዜ እንደሚወስድ የሚጠበቅ ቁልፍ ሃብት አለ:: እርሱም ሃብት መሆን የሚችል ሰው ነው! ሃብት የሆነ ሰው! ሃይል የሆነ ሰው!! Human capital!!! በኢትዮጵያ ውስጥ የትውልድ ክፍተቱ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ሃብት::

### የትውልድ ክፍተት

የትውልድ ክፍተት ባለባት ሀገር ውስጥ ሃብት የሆነ ሰው በተቋማት ግንባት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ በምን ሊተካ ይችላል? በምንፈልገው እና እየሆነ ባለው ውስጥ የትውልድ ክፍተቱ ምን ያህል ዋጋ እያስከፈለንስ እንደሆነ መረዳታችንስ ምን ያህል ነው?

በአሜሪካ የማልያው ለውጥ ከሪፐብሊካን ወደ ዲሞክራት መሆኑ ሲታሰብ ምን ይፈጠር ይሆን የሚለው ስጋት ጠመንጃ ከሱቅ እንድትገዛ ያደርግ ይሆናል እንጂ ተቋማቱ ሚናቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ ብሎ በማሰብ አሜሪካኖች ወደ ሜክሲኮ ሲሸሹ ወይንም የእንግሊዝን ኢሚግሬሽን ሲያጨናንቁ ማየት ዘበት ነው::

ኢትዮጵያችን ንጉሳዊ ስርዓቱን ወደ መዝገብ ቤት ልካ በወታደር እጅ እጣ ፋንታው ሲወሰን በድንገቴ ስልጣን ከእጁ የገባው ወታደር እንዲገደሉ የወሰነባቸው ዜጎችን በፍርድ አደባባይ ይዞ በመገኘት፤ ለተቋማት ግንባታ እድሉን መጠቀም ሲኖርበት በተቋማቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ረሽኖ ቀበራቸው:: ሙታቸውን ለመቅበር ለወደዱትም ይህን ማድረግ እንዳይችሉ አዋጅን አስነገረ:: ስለ ሀገር የወጡ የወረዱ አንገታቸውን ደፉ:: አዲሱ ስርዓት ስለ መቀመጫው መደላደል ብሎ የትውልድ ክፍተትን በምድሪቱ ላይ አስፍኖ ኢትዮጵያ የቁልቁለት ጉዞውን አስተማማኝ ባልሆነ ▶

ፍሬን ትወርደው ዘንድ የመጀመሪያው ጥይት ተተኮሰ፡፡ "ፖለቲካና ኮረንቲ" ከሩቁ የሚለው ያልተጻፈው ሕግ እውን ይሆንም ዘንድ መንገዱ ተከፈተ፡፡ ስደትም በሁላችን ጓዳ ድንኳኑን ተክሎ ቤተሰብ ልጆቹን በስደት አጥቶ መንፈሱ ተከፋፈለ፡፡

ወታደሩን ያስወገደው ሌላኛው ወታደር ማልያውን ሲቀይርም የአፈጻጸም ለውጡን አድርጎ ሃብት ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን እኔ ያሰብኩትን አላሰባችሁም ብሎ የመስዋዕት በግ አድርጎ አቀረባቸው፡፡ ራእይ አልባ ሆነው እንዲኖሩም የስደት በርን ወለል አድርጎ ከፍቶ እስከ ቦሌ አየር ማረፊያ ሸኛቸው፤ በሀገሪቱም እንዳሻው የሰው ደም ከክረምት ዝናብ የቀለለበትን ፖለቲካዊ ኪሳራ የምናይባቸውን ቀናት አዘጋጅቶ አቀረበልን፡፡ ዛሬም የትውልድ ክፍተቱን በር የሚዘጋ ጠፍቶ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተስፋ አድርገው ቀኝ እግራቸውን ለማስገባት የዳዳቸው ወደ ኋላ እንዲሉ እየተገደዱ እያየን እምነት የሚጣልባቸው ተቋማትን የማግኘት ህልማችን "ላም አለኝ በሰማይ ሆኖ" ይሰማናል፡፡ የትውልድ ክፍተት!!!

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር ውስብስብ አጀንዳዎች ሳይሆኑ ውስብስብ ግለሰቦች ናቸው ብንል ያጋነንን አይመስለኝም፡፡ አጀንዳው ቀላል ሆኖ አጀንዳውን ከእጃቸው ያደረጉ ሰዎች ካወሳሰቡት የሰው ጉዳይ ቀዳሚው አጀንዳነት መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ እውቀትና ጥበብ የጎደለው አካሄድ ውስጥ እንደ ሀገር መገኘታችንን ስናስብ የጎደለንን እውቀትን ሆነ ጥበብ ለክተን መፍትሄ ፍለጋው ላይ ካልወጣን ተራ የመዞር ጉዞዋችንን ከወደ ተራራው ጫፍ ወደ ቁልቁለት ይሆናል፡፡ መቀበል እንጂ መስጠት አለመቻል የፖለቲካችን መገለጫ ሲሆን እንዴት በእዚህ ዘመን እንዲህ ይታሰባል ብለን የትወልድ ክፍተቱን መመርመር የለብንም? ከአንድነት ይልቅ ልዩነት የሚሰብኩ አደባባዮችን ሞልተው ስናይ በአድዋ መንፈስ የፓን አፍሪካ መንፈስ አነቃቂያዎች ዝምታን መርጠው ስናይ የኪሳራው ጥልቀት እንዴት ከትውልድ ክፍተት ባነሳ ቃል ሊገለጽ ይችላል? የተማረውም ሆነ ያልተማረው፤ ባለሃብቱም ሆነ ድሃው እኩል በስደት በር ላይ ሲገናኙ የነገራችን ውል እየተወሳሰበ መሆኑን መረዳት እና ስለ መፍትሄውም የትውልድ አባትና እናት የሚሆኑትን ማማተር እንዴትስ ሊጠፋብን ይችላል? የአንድ ሰው ዋጋ ከየትኛውም ቁስ በላይ መሆኑን ተረድቶ ሰው፣ ሰው መሸተት ሲሳነን አወዳደቃችን እኛው በእኛው መሆኑን ተገንዝበን ባለመድኃኒት የሚሆን ሰውን ፍለጋ መውጣት እንዴትስ አቃተን? ለሁሉም ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ባልሞክርም ፈረሱን ከጋሪው ለያይቶ ለማየት ግን ጊዜው አሁን ነው እላለሁ፡፡ በትውልድ ክፍተት በምታምጥ ሀገር ውስጥ ፈረሱና ጋሪው በአግባቡ ሊተረጎሙ ይገባል፡፡

## ፈረሱና ጋሪው ...!

በኢትዮጵያችን ልናይ የምንወደውን ለውጥ በምናስብበት ጊዜ እየጠየቅን ያለነው የተቋማት ግንባታን ነው፡፡ የተቋማት ግንባታ ለኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ያለንበት የትውልድ ክፍተት መደገፊያ የሚሆኑ የዲሞክራሲ ተቋማትን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ሊፈጅ ይችላል የሚለው ላይ ተቀራራቢ ምልከታ ሊኖር ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ የትውልድ ክፍተት፣ ተቋማት ግንባታን በአጭሩ ማምጣት አስቸጋሪ እያደረገው እንዳሉ ምልክቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ ምርጫ ቦርድን የሚያህል ትልቅ ሀገራዊ ተቋም የሚፈልገውን የሰው ሃይል በገብያ ዋጋ ሀገር ማቅረብ ሳትችል ቀርታ ምርጫው ለኢትዮጵያውያን ገንዘቡ ደግሞ ከሌሎች ሆኖ ስናይ ከተቋማት ግንባታ ጀርባ ያለው ሃይል የሆነውን ሰው ከሰው ሃይል ገብያ ማግኘቱ ለኢትዮጵያ ቀላል አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንን በተመለከተ ፓርላማው ረጅም ሰዓት ወስዶ የተጨቃጨቀበት (የተወያየበት ከማለት የተጨቃጨቀበት ብንል ይቀላል) አንቀጽ ምን እንደሆነ ስንመለከት ትልልቅ ተቋማት የሚፈልጉቸው አይነት ሰዎችን ለማግኘት መቸገራችንን የሚያስረዳ ነው፡፡

ፈረሱ፣ ተቋማትን እውን ማድረግ የሚችል የሰው ሃይላችን ሲሆን ጋሪው ደግሞ ተከትሎ የሚመጣው ወይንም የምንጠብቀው ውጤት ይሁንና ከፈረሱ ጋሪውን ደጋግመን እናስምርበት፡፡ ያለሰው ሃይል ሊፈጠር የሚችል ጠንካራ ተቋም የለም፡፡ በኢትዮጵያ ቢሮክራሲ ውስጥ የሚፈለገው የሰው ሃይል ብዛት እና ከሀገሪቱ ገብያ የሚገኘው ለቦታው የሚመጥነው ሰው አራምባና ቆቦ ከሆኑ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ ሁለተኛ ብንሆንም ተቋማትን መሸከም የሚችሉ ሰዎችን በማብቃት ረገድ ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጉዟችንን የኤሊ አድርጎታል፡፡ ፍላጎታችን እና መሆን በቻልነው መካከል ልዩነቱ ገዝፎ የሚታይ ነው፡፡ ከእዚህ ጀርባ ያለፍንባቸው ስርዓቶች በአሉታዊነት ያበረከቱት የትውልድ ክፍተት ቀዳሚው ምክንያት ይሆናል፡፡ ኢዜማን እንደ ድርጅት በመመስረት እና ከ 400 በላይ በሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች ላይ መገኘትን እንደ አንድ ግብ አይተን በተራመድንበት ጉዞ ውስጥ በስኬት የምንቆጥረው ብዙ ድሎች ቢኖሩንም የመዋቅራችንን ጥራት ከሰው ሀብት አንፃር ስንለካው ረጅም መንገድ መጓዝ እንዳለብን ያሳየናል፡፡ ተቋማት መጠንከር ሳይችሉ ሲቀር ግለሰቦች ተቋም ይሆኑና ግለሰቦቹ ሲኖሩም ሆነ ሳይኖሩ ችግር መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል፡፡

ንጉሳዊ ሰርዓቱንም ሆነ ወታደራዊ መንግሥቱን ገዝግዞ የጣለው ውጫዊው ጠላት ሳይሆን ውስጣዊ ድክመት መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ ኢሕአዴግም ውስጥ የሆነውን ንቅዘት መገለጫው ሃብት የሚሆኑ ሰዎችን ማጣት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ችግሩ በቤተመንግሥት ሆነ በቤተክህነት ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ መፍትሄ ፍለጋውን ሀገራዊ ማድረጉ የሚሻል ይመስላል፡፡ መፍትሄ ፍለጋው ችግሩን በችግርነት በመቀበል ላይ የሚጀምር ነው፡፡ እነሆ ቀዳሚው ችግር የጣይቱ እና አቢጌል ወንበር በኢትዮጵያ ከተሰበረ የመከረሙ የሚታወቅ መርዶ፡፡

## የጣይቱ እና አቢጌል ወንበር

የትውልድ ብያኔ ስናነሳ በትውልድ ውስጥ ቁልፍ ሚና ኖሯቸው ስለሚያልፉ ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ባለሙያዎች ወዘተ ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡ አንድ ትውልድ ስኬቱም ሆነ ውድቀቱ የሚታየው ዜጎቹ በተሰማሩበት ዘርፍ፣ በወሰዱት ኃላፊነት እና በሆኑት ሁናቴ ውስጥ ነው፡፡ ለዛሬ በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ እውቀትን ወደ ጥበብ በማሻገር የተዋጣላቸው ስለሆኑት ጣይቱ እና አቢጌል ወንበር ጥቂት እንበል፡፡ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ፖለቲካ የትውልድ ቅብብሎሽ ችግሩን ያሰፋው ምክንያት እንደሆኑ ከማስባቸው ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው የትውልድ ማህጸን የሆኑት ሴቶች ወንበራቸው መሰበሩ ነው፡፡ የሴት እህቶቻችን የፖለቲካ አስተዋጽኦን ጠመንጃ አንስቶ መግደል በመቻል ውስጥ በተበየነ የፖለቲካ ትርጉም ውስጥ ሴት እህቶቻችንን የጎደሉበት ማኅበር እንድንጠጣ አድርጎናል፡፡

ለወ/ሮ አቢጌል ደብዳቤው የተላከው ከውድ ባለቤቷ ነበር፡፡ ይህ የአቢጌል የትዳር አጋር ካሉት ልምዶች መካከል አንዱ ከሚስቱ ጋር የመመካከር ልምድ ነው፡፡ የሚያስበውን ይነግራታል የምታስበውን ትነግረዋለች፡፡ የእዚህ ሰው አማካሪ ተደርጋ ስሟ በመዛግብት የሰፈረችው እቺ ሴት ወ/ሮ አቢጌል አንዷ የአሜሪካ አገር-መንግስት ምስረታ መንገድ ጠራጊዎች መካከል ስሟ ደምቆ የሚጠራ ነው፡፡ እርሷ የጆን አዳምስ ሚስት አቢጌል ነች፡፡ የመጀመሪያው የአሜሪካ ምክትል ፕሬዝዳንት ወይንም የሁለተኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የነጻነት ጉዞው ትግል አስገምጋሚ የቁርጠኝነት ድምጽ ባለቤት የጆን አዳምስ የትዳር አጋርና አማካሪ፡፡ አቢጌል በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ሚስቶች ያላቸውን ሚና ፍንትው አድርጋ የምታሳይ ሴት ነች፡፡ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ፖለቲካ ውስጥ በጥበብነት መገለጽ የተሳነውን እውቀትን ወደ ጥበብነት ለመቀየር ምክር ያላት የእቴጌቱ ጣይቱ አምሳያ፡፡

ሴቶች በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚናን ለመዘከር የአንድ ግብረሰናይ ድርጅትን ፈንድ እስኪገኝ መጠበቅ ከራስ ጋር መጣላት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የቅርብም ሆነ የሩቅ ፖለቲካ ውስጥ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ያደረጉ እንስቶች ብዙ ናቸው፡፡ የታሪክ ዘጋቢዎች ሚዛኑን በአግባቡ መመጠን ያለመቻል ችግር የሴቶች ብልሃት የተጋባው ፖለቲካን ለማጣት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የትውልድ ክፍተት ያለበት ፖለቲካችን ሲነሳ ሊነሳ የተገባው የመጀመሪያው ቁልፉ ነጥብ በፖለቲካችን ውስጥ ሁላችንም አለንበት ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ሁላችንም አለንበት ወይን እጅግ ለማጥበብ ሞክረን የሴቶችን ስልታዊ ተሳትፎን ማጣት የትውልድ ክፍተቱን እያሰፋው የሚሄድ እውነታ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ፖለቲካ ለእኔ ትውልድ የሴቶች ተሳትፎ በስልታዊነት የሚገለጥበት ነው፡፡ ፖለቲካ ለእኔ ትውልድ የጣይቱ-አቤጌልን ወንበር መጠገን መቻልን የሚጠይቅ ነው፡፡ ፖለቲካ ለእኔ ትውልድ የትራምፕን በትረ ሥልጣን በቃህ ብለው የባይደን ወንበርን በማስገኘት ውስጥ የአሜሪካ ሴቶች የተጫወቱትን ሚናን በኢትዮጵያን እውን እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ የተረጋጉ ተቋማትን ማንበርም ሆነ ህይወት ዘርተው እንዲተነፍሱ ለማድረግ የሴት እህቶቻችን ድርሻ ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ የአሜሪካ እንስቶች ትራምፕን አውርደው ባይደንን ለማውጣት የተሰለፉት ሰልፍ ክስተቱ በድንገቴ አለመሆኑን አስምሬ የእኛን ፖለቲካ የትውልድ ቅብብሎሽ ስለጎዳው ሁለተኛ ነጥብ ማለትም ድንገቴነት እናንሳ፡፡

## ድንገቴነት

ህምምም.... (መገረሜ ይሰማልኝ)፡፡ አንባቢ ሆይ የኢትዮጵያ የቅርብ ዘመን ፖለቲካ በአጭሩ የድንገቴ ፖለቲካ መሆኑን አስበህ ታውቃለህ? ወታደሩ ሀገር እመራለሁ ብሎ ሳያስብ በድንገት ሥልጣን ከእጁ ገባ፡፡ በድንገት እጁ የገባውን ሥልጣንም ለማክረም ሲል በእጁ ያለውን ጠመንጃ ተጠቀመ፡፡ ሕወሓት በተጋሩነት መንፈስ ተቃኝታ ወደ ፊት ግፋው ስትል ከርማ ድንገት ኢትዮጵያ በሚል ካርታ ላይ ራሷን አግኝታ በድንገት እጇ የገባችውን ኢትዮጵያ በዘመቻ ጋጋታ ለ 27 አመታት መራች፡፡ ከድንገቴ ሥልጣን ጀርባ ግን የሕዝብ ትግል ነበረ፤ አሁንም አለ፡፡ የተማሪው የለውጥ ጥያቄ ወታደሩን በቆረጣ እንዲገባ ሲያደርገው፤ የሕዝብ በወታደሩ መማረር በሽምቅ ጦርነት የተካኑት አራት ኪሎ ሲያደርሳቸው፤ በወጣቶች እንቅስቃሴ የብልጽግናን ስብስብ በድንገቴነት በቤተመንግሥቱ ቀይ ምንጣፍ ላይ እግሮቹ እንዲራመድ ሲያደርገው ይህ ድንገቴነት ተቋማትን እያጠፋ፣ የትውልድ ክፍተትን እያሰፈ አምባገነኖች እንዲወለዱ ምክንያት ስለመሆኑ ምን ያህል አስተውለናል?

ጠንካራ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ስልጣን በሕዝብ አመጽና በድንገቴነት ከአንዱ ወደ አንዱ መምጣቱ የሚገርም አይሆንም፡፡ ችግሩ ሁሌ አፍርሶ መትከል መሆኑ ነው፡፡ ችግሩ የትውልድ ክፍተትን እያሰፋ መሄዱ ነው፡፡ ችግሩ የታሪክ መዝገብ ውስጥ በደም የጨቀዩ ገጾችን ማብዛቱ ነው፡፡ ችግሩ ሀገርን የስደት ኮሪደር ማድረጉ ነው፡፡ ችግሩ ብዙ ነው! መፍትሄ ፍለጋው ላይ እንደ ትውልድ መቆሙ አስፈላጊ መሆኑን ከተረዳን ፖለቲካ ለእኔ ትውልድ ምን መምሰል እንዳለበት በማንሳት የመፍትሄ ምልከታዎቼን ላቅርብ፡፡

## የመፍትሄ ምልከታ

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከ1960ዎቹ የተማሪዎች ትግል በኋላ ወደ ሁለተኛው ምእራፍ እንደተሸጋገረ የዚህ ፅሁፍ ፀኃፊ ያምናል፡፡ ሁለተኛውም ምእራፍ ማለት ከሕወሓት መሩ ኢህአዴግ የ27 ዓመት አገዛዝ ማክተም ጀምሮ ያለው ነው፡፡ የሕወሓት መሩ ኢሕአዴግ በብዙ መለኪያዎች የ1960ዎችን ትውልድ እንደትውልድ ይወክላል ብዬም አምናለሁ፡፡ ሁለተኛው ትውልድ እድለኛም እድለ ቢስም ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡ እድለኝነቱ ከትላንት ለመማር ከፈቀደ ከቅርብ ዘመን ፖለቲካችን ግድፈቶች የመማር እድል ያለ መሆኑ ነው፡፡ እድለ ቢስነቱ ለኢትዮጵያ ለመድረስ ለመሞከሪያ የሚሆን ጊዜ እንደ መጀመሪያ ትውልድ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ የመጀመሪያው ትውልድ በጠመንጃም ሆነ ምርጫን አጭበርብሮ እንዳሸው ለመሆን በብዙ መንገዶች ሊሆን የተገባውንም ሆነ ያልተገባውን አዳቅሎ ሞክሯል፡፡ ሁለተኛው ትውልድ ግን እንደ መጀመሪያው ትውልድ ለኢትዮጵያ ለመድረስ የመሞከሪያ ጊዜ የለውም፡፡ ያለው ኢላማውን አስተካክሎ ወደ ውጤት የሚቀየር ሥራ ላይ ማተኮር ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ውጤት ሊደርስ የሚችልን ሥራን መስራት፡፡ እርሱም ሰው ላይ መስራትን ከሁሉም የሚቀድም ማድረግ፡፡

የ1960ዎቹ ትውልድ በድንገት እጁ የገባውን ለውጥ እንደ ትውልድ ማስተናገድ ሳይችል የአገሪቱ ፖለቲካ መረጋጋት ሳይችል 50 አመታት ማለፉን ስናስብ መቆጨት ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሁለተኛው ትውልድም በእጁ የገባውን እድል እንደትውልድ እንዳያባክን በኃላፊነት ስሜት ለውጡን ሊመራ እንደሚገባ ማሰብ አስተዋይነት ነው፡፡ ከ 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ያለችው ኢትዮጵያ መልክ በተወሰነ ደረጃ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያ መልክ አድርገን ልናቀርባት እንችላለን፡፡ ይህ ትውልድ እንደ ትውልድ በመነጋገር የሚያምን፣ ወደ መካከለኛ መንገድ ለመምጣት አቅም ያለው፣ ሰጥቶ ለመቀበል የሚደፍር፣ እኔ እኔ ከሚል አጉል የንፋስ ጉሽማ ወጥቶ ከፍ ብሎ የሚያስብ ወዘተ እንዲሆን በብርቱ መመኘት እና እንዲሆን ማድረግ የሁለተኛው ትውልድ የማትረፊያ መንገድ ነው፡፡

ከ27 ዓመቱ ሕወሓት መር ኢሕአዴግ በኋላ የሚመጣው አገራዊ ምርጫ እንደ ሀገር ትልቅ ትርጉም ያለው በኢትዮጵያ ታሪክም ውስጥ የራሱ በርካታ ክስተቶችን ይዞ የሚመጣ ምርጫ ነው፡፡ ይህ ምርጫ አንድ ተራ የምርጫ ዙር ሳይሆን ሁለተኛው ትውልድ ኢላማውን ሳይስት ውጤት የሚያስቆጥርበት፤ በድርድርም ሆነ በካርድ ፖለቲካዊ ህመሞችን ለመፈወስ ዝግጁ መሆን እንዳለበት የሚያስረዳበት ምርጫ ነው፡፡ መጪው ምርጫ እና ከምርጫው በኋላ እንደሚሆን የሚጠበቀው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ የእዚህን ትውልድ በንቃት ነገሮችን መከታተል የሚጠይቅ፣ በታሪክ ውስጥ እንደ

ትውልድ ከሚመጣ ወቀሳ ራሱን ለማዳን ፖለቲካ ለእኔ ትውልደ ምንድን ነው ብሎ ራሱን ጠይቆ አውዳዊ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ሊያደርግ የሚገባው ነው፡፡

የሃሳብ ልዩነቶችን ለመፍታት የምንሄድበት መንገድ ውስጥ ያለው ፈተና ቀላል ባይሆንም ሰጥቶ ለመቀበል በእውቀት ዝግጁ መሆን፤ በጥበብ ነገሮችን ማድረግም ይጠይቃል፡፡ እርግብ መሆን ጥሩ ነው፤ ነገር ግን እርግብ መሆን ብቻ አያዋጣም፡፡ እባብ ውስጥ ያለውን ብልሃትም ታሳቢ ማድረግን ወቅቱ ይጠይቃል፡፡ በእባብ ብቻም እወጣዋለሁ ማለት ተራራን በሰፌድ እንደ መግፋትም ይሆናል፡፡ የትውልድ ክፍተቱን ታሳቢ ያደረገ፤ ሃይልን በሚገባ አሰባስቦ ታሳቢ የሚደረገውን ውጤት ማሳካት የሚቻልበት መፍትሄ ያሻናል፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አፍጠው እየወጡ ያሉ አጀንዳዎች ውስብስብ ናቸው ተብሎ መታሰብ የለበትም፤ ለመደማመጥ መሞከር እንጂ፡፡ አጀንዳዎችን በበሰለ አካሄድ ተወያይቶ በዲሞክራሲያዊ መንገድ እልባት እያገኙ እንዲሄዱ በማስቻል ወቅቱን ሳይረፍድ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ እዚህ ጋር ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባት እንደ መፍትሄ መወሰዱ ትክክል ነው፡፡ ተቋማትን ከመገንባት ባሻገር ግን ለማንኛውም ውሳኔ ራስን ዝግጁ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡ በዲሞክራሲያዊ ጉዞ በምንም ነገር አልደራደርም የሚል አካሄድ የትም እንደማያደርስ መረዳት አንዱ ራስን ዝግጁ ማድረጊያ አቅጣጫ ነው፡፡ በማንኛውም አጀንዳ ላይ መወያየት፣ መመካከር፣ መግባባት የማይቻል ከሆነ በዲሞክራሲያዊ አግባብ ሕዝበ ውሳኔ ማድረግ እና ለሚሰጡ ድምጾች ተገዥ መሆን የሰለጠነ ፖለቲካ ልምምዳችንን መንገዱን ያቀናዋል፡፡

ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲኖር የታገሉ ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለሚሰጠው ውጤት ምን ያህል ተገዢ ይሆናሉ የሚለው ግን ዛሬም ጥያቄ ሆኖ የእዚህን ትውልድ ፖለቲካም መፈተኑን የሚቀጥል ይመስላል ፡፡ ሁሉም ራሱ እንዲሆን የሚፈልገውን በልቡ ይዞ ‹‹የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው›› የሚል አካሄድን የሚመርጥ ከሆነ የትውልድ ክፍተቱ እየቀጠለ አደጋውም እየሰፋ መሄዱን ለመናገር ነቢይ መሆንን አይጠይቅም፡፡ ይህ ትውልድ ራሱን ለእዚህ ፈተና ማዘጋጀት አለበት፡፡ እኛ ኢዜማዎችም ዲሞክራሲን በተግባር በቤታችን በመለማመድ ለሀገር የመትረፍ ጉዞዋችንንም ማጠናከር አለብን፡፡

የታሪክ ሊቁ ሪቻርድ ሞሪስ እ.ኤ.አ በ1973 የአሜሪካ መንገድ ጠራጊ ሰባት መስራች አባቶችን ዘርዝሯል፡፡ እነርሱም ጆን አዳምስ፣ ቤንጃሚን ፍራንክሊን፣ አሌክሳንደር ሐሚልተን፣ ጆን ጄይ፣ ቶማስ ጀፈርሰን፣ ጀምስ ማዲሰን እና ጆርጅ ዋሽንግተን ናቸው፡፡ መንገድ ጠራጊዎች የራስን አገር ነፃ በማውጣት ጉዞ ውስጥ ተበይነዋል፡፡ ዛሬም ኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲ፣ ነፃነት፣ እኩልነት እና ፍትሃዊነት ለመድረስ የምታደርገው ጉዞ የሀገር ምሶሶ የሚሆኑ ትውልድ ወካዮችን ትፈልጋለች፡፡ ትውልዱ ስለ ውድቀታቸው የሚከሳቸው ሳይሆን በጥበብና በእውቀት ስለ ሀገር በመኖራቸው የሚኮራባቸው፡፡ የትውልድ ክፍተቱን ሞልተው፤ የዘመናቸውን ፖለቲካ በሚገባ ኖረው የሚያልፉ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ አዋላጆች፡፡ እኔ ግን ዛሬም የተቋማት ግንባታው ፖለቲካ ለእኔ ትውልድ ትርጉም ኖሮት ሃብት በሆኑ ሰዎች ላይ እስኪመሰረት እናፍቃለሁ፡፡እነዚህን ሰዎች ወልዶ ማሳደግ ላይ ሊሰራ የሚገባው ብዙ መሆኑን ሳልክድ የተሻለ ሀሳብ ቢዘገይም ይገዛልና፤ ስለተሻለ ሀሳብ ዛሬ እንኑር፡፡ ፍሬውን ነገ እናጭዳለንና!

መልካሙን ሁሉ!





# ‹‹አላማችን ነገ ሀገራችንንና ፓርቲያችንን የሚረከቡ ወጣቶችን ማብቃት ነው››

## ፅዮን እንግዳዬ፣ የኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ

ህዳር 16 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት የተዘጋጀው ‹‹የኔ ፖለቲካ›› የወጣቶች የውይይት መድረክ ሐሙስ ሕዳር 17 ቀን 2013 ዓ.ም በኢዜማ ዋና ፅህፈት ቤት በመስፍን ወልደማርያም አዳራሽ ከቀኑ 11፡00 ጀምሮ እንደሚካሄድ የኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ ፅዮን እንግዳዬ ለዜጎች መድረክ አስታወቁ፡፡

ስለ ውይይት መድረኩ አላማ የዜጎች መድረክ ለወጣቶች ጉዳይ ተጠሪዋ ፅዮን እንግዳዬ ላቀረበችላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የውይይቱ መሰረታዊ ዓላማ የሀገሪቷ ወጣቶችና የኢዜማ ወጣት አባላትን በእውቀት በማነፅ በሀገራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ክህሎትን እንዲያዳብሩ በማድረግ ሀገሪቷን እንዲሁም ፓርቲያቸው ኢዜማን የሚረከቡ ወጣቶችን ማብቃት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ‹‹ወጣቶች ፖለቲካን እንዴት ይረዱታል የሚለውን እንደመነሻ ሀሳብ በማድረግ የንግግር ብቃታቸውን የሚያዳብሩበት፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ወጣቶችን እንዲመለከቱ የሚረዳ ብሎም በሁሉም ዘርፍ ክህሎታቸውን የሚያሳድጉበት መድረክ ነው›› ያሉት ተጠሪዋ በመድረኩ ላይ ወጣቶች የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን እንዲያንሸራሽሩ በማበረታታት የመወያያ መድረኩ የሀሳብ ልውውጥ የሚካሄድበት ይሆናል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ለመሳተፍ ጥያቄ ያቀረቡት ወጣቶች በርካቶች መሆኑን የጠቀሱት የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪዋ፣ አሁን ያለው የኮቪድ 19 ወረርሽኝና ሀገራዊ የጸጥታ ሁኔታዎች ተዳምረው የመጀመሪያውን ዙር ውይይት የዓለም አቀፍ ኮቪድ መከላከያ ዘዴን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በአነስተኛ የወጣቶች ቁጥር ለማካሄድ እንደሚገደዱና በቀጣይ ወራት በሚደረጉ መድረኮች ግን ከሌሎች ፓርቲዎችም ጭምር ለተውጣጡ እንዲሁም በውይይት መድረኩ ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ ወጣቶች ሁሉ መድረኩ በአወያይነትም ሆነ በተወያይነት ለመሳተፍ ክፍት እንደሚሆን ተጠሪዋ አስረድተዋል፡፡

‹‹የኔ ፖለቲካ›› የውይይት መድረክ ወሩ በገባ በሶስተኛው ሳምንት በሚውለው ሐሙስ በወር አንድ ግዜ የሚካሄድ የውይይት መድረክ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ‹‹የመሬት ወረራውን ችግር የመፍታት ፍላጎት ካለ ከባለድርሻ አካላት ጋር የይስሙላ ሳይሆን የምር ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል››

## ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ

ህዳር 16 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከመሬት ወረራ ጋር በተገናኘ ይፋ ያደረገው ጥናት ችግሩን በደንብ የማይገልፅና አጥፊዎቹን አካላት በግልፅ ያላስቀመጠ ሆኖ እንዳገኙት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ያለአግባብ መሬት የወሰዱ አካላት መሬታቸው እንዲነጠቅ ኢዜማ ከመሬት ወረራና ከኢፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እደላ ጋር በተገናኘ ባጠናው ጥናት ጥያቄ አቅርቦ እንደነበር ያስታወሱት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ይህንን በሚያመላክት መልኩ የከተማ አስተዳድሩ መፍትሔ እየሰጠ አይደለም ብለዋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ ባጠናው ጥናት ከ1352 ሔክታር በላይ መሬት በሕገ ወጥ መንገድ ተወሮ መያዙን ይፋ አድርጓል፡፡ በሕገ ወጥ መልክ መሬት በያዙ አካላት ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ ከተማ አስተዳደሩ አስታውቋል፡፡

ይህንን በሚመለከት ከዜጎች መድረክ ለተነሳው ጥያቄ ዋሲሁን ተስፋዬ ሲመልሱ፣ የቀረበው ጥናት ላይ ‹‹እርምጃ እንወስዳለን›› መባሉን ጠቅሰው የከተማ አስተዳደሩ ኃላፊዎች ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ አካላት እንደመሆናቸው መጠንም እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡ የመሬት ወረራው የከተማው አስተዳደር ባለው ደረጃም ብቻ እንዳልሆነም ጠቁመዋል፡፡ በመሬት ወረራው ላይ ወረዳ ላይ ከሚገኙ ግለሰቦች ጨምሮ እስከ ከፍተኛው የመንግሥት ስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች እጃቸው መነከሩን የጠቆሙት ኃላፊው የከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ያሉ አካላት ሳይቀር በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ ‹‹ትላልቆቹን አሳዎችን ከግምት የከተተ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዱ ይሆናል ወይ የሚለውን የምናየው ነው የሚሆነው›› በማለት ሕጋዊ እርምጃው በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ ሰዎችንም መንካት እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

‹ በተግባር ያየነውም ከመሬት ወረራ ጋርም ሆነ ከኢፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች



እደላ ጋር በተገናኘ እጃቸው አለባቸው ተብሎ የሚጠረጠሩ ሰዎችን ከአንድ ቦታ በማንሳት ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወሩ ነው ሲደረግ የነበረው›› ያሉት ዋሲሁን ተስፋዬ ከላይኛው የመንግሥት ስልጣን ላይ የሚገኙትን አጥፊዎች በመለየት የመቅጣት ብቃቱም ሆነ ሞራሉ ከተማው አስተዳደር ኃላፊዎች አላቸው ብለው እንደማያምኑ ገልፀዋል፡፡
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይፋ ያደረገውን የጥናት ግኝት በተመለከተ ከከተማ አስተዳደሩ እና ከፌደራል ተቋማት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም የተለያዩ ሀይማኖት ተቋማት ተወካዮች የመሬት ወረራ መንስኤ እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ዙሪያ ሰፊ ውይይት አካሄዶ ጥናቱን ይፋ እንዳደረገው አስታውቋል፡፡

ኢዜማ በመሬት ወረራ ላይ ጥናት እንደማድረጉ መጠን እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ጥሪ ተደርጎለት ጥናቱ ይፋ ከመደረጉ በፊት በጥናቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር ወይ? በሚል ዜጎች መድረክ ለድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ዋሲሁን ተስፋዬ ጥያቄ አቅርባለች፡፡

ኃላፊው በምላሻቸው ኃላፊነት የሚሰማው የመንግሥት አካል መውሰድ ያለበትን ኃላፊነት ፓርቲያቸው በመውሰድ በከፍተኛ ፈተና ውስጥ አልፎ ጥናት ማካሄዱን ገልፀው፤ በዚህ ደረጃ ጥናት ያካሄደ አካል እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ተጠርቶ በዚህ ጥናት ላይ ያለህ አስተያየት ምንድነው ሊባል ይገባው እንደነበር ጠቁመው፤ ከተማ አስተዳደሩ በጥናቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዳልጠየቃቸው ተናግረዋል፡፡

‹‹እንደ አንድ የከተማው ነዋሪም ሆነ እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲም ባለድርሻ አካል ነን፡፡ የጉዳዩ ባለቤቶች እነማን ናቸው ብሎ ጠይቆ እነሱኑ ለይቶ ከእነሱ ጋር ውይይት የማድረግ ፍላጎት የለም፡፡ አልተደረገምም፡፡ ጥናታችንን ከሰጠናቸው በኋላ ይህንን ጥናት አይተን ከእናንተ ጋር ውይይት እናደርጋለን ብለውን ነበር፡፡ ከእኛ ጋር ግን አልተወያዩም፡፡ ባለድርሻ አካላት ብለው ከእነማን ጋር ውይይት እንዳደረጉ አናውቅም፡፡ ለእኛ ጥቆማ ያቀረቡ እንዲሁም ተጎጂ የሆኑ አካላትንም ያሳተፈ ውይይት ነው ያካሄዱት ማለት አይቻልም፡፡ ›› ሲሉም ላቀረብንላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን ሰንዝረዋል፡፡

የመሬት ወረራውን ችግር የመፍታት ፍላጎት ካለ ከባለድርሻ አካላት ጋር የይስሙላ ሳይሆን የምር ውይይት ማድረግ እንደሚገባ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ አሳስበዋል ‹‹ችግሩን ከላይ ከላይ ብቻ የሚነካ ጥናት በማቅረብ መሰረታዊውን ችግር መፍታት አይቻልም፡፡ ችግሩን ከሥረ መሰረቱ ለመፍታት አጥፊውን አካል ለይቶ ያጠፋውን አካል የጥናቱ ውጤት በደረሰበት ድምዳሜ መሰረት በመቅጣት አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ሲቻል ብቻ ነው መፍትሔ ማምጣት የሚቻለው ብዬ አምናለሁ፡፡›› በማለት መፍትሔ ይመጣል ብለው የሚያስቡበትን መንገድ ጠቁመዋል፡፡ ችግሩን መፍታት ከተፈለገም ኢዜማ አስቀድሞ ባቀረበው ጥናት ላይ ለመወያየት በሩ ክፍት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከመሬት ወረራና ኢፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እደላ ጋር በተገናኘ አጥንቶ ይፋ ያደረገውን ጥናት ተከትሎ በዋና ፅህፈት ቤቱ መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆኑ ዜጎችና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ባሉበት የፓናል ውይይት ለማድረግ አቅዶ የነበረ ቢሆንም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውይይቱን ማካሄድ አትችሉም ብሎ በጻፈው ደብዳቤ የተነሳ ውይይቱን ሳያካሄድ እንደቀረ አይዘነጋም፡፡

ከተማ አስተዳደሩ ሕገ መንግሥታዊ የሆነውን የመሰብሰብ መብት በመግፈፉም ኢዜማ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወስዶታል፡፡ መዝገቡ የተከፈተበት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ የፍትሐብሔር ችሎትም የከተማ አስተዳደሩ የቀረበበት ክስ ላይ ምላሹን ይዞ እንዲቀርብ ለሕዳር 22 ቀን 2013 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡





# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ያለው ፓርቲ ከዚህ ቀደም የሚያገኘው የአየር ሰአት ከ60 በመቶ ወደ 5 በመቶ እንዲቀንስ በፓርቲዎች መካከል ስምምነት ላይ ተደረሰ

ህዳር 16 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባዘጋጃቸው የተለያዩ መመሪያዎች ዙሪያ ከተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አርብ ሕዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም ውይይት ማድረጉን በውይይቱ ላይ የተካፈሉት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የውይይቱ አላማ ከፓርቲዎች የሚሰጡ ግብአቶችን ለማካተት እና ቦርዱ ያዘጋጃቸውን መመሪያዎች ለማስተዋወቅ የነበረ ሲሆን በእለቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የአየር ሰአት ድልድል መመሪያ ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሚዲያዎች ጋር ውይይት መደረጉንም ምክትል ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡ የአየር ሰአት ድልድል ቀመር፣ ድልድሉ ከዚህ በፊት የተካሄደበት መንገድ እና የድልድሉ ማከናወኛ ቴክኖሎጂ በቦርዱ እና በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን በኩል ቀርቦ እንደነበረ ምክትል ሊቀመንበሩ አስረድተዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ያለው ፓርቲ ከዚህ ቀደም የሚያገኘው የአየር ሰአት ከ60 በመቶ ወደ 5 በመቶ እንዲቀንስ በፓርቲዎች መሀል ስምምነት ላይ መደረሱን የጠቆሙት ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) ለአየር ሰአት ድልድሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ መስፈርት በተጨማሪ በእኩል የሚደለደሉ ሌሎች መስፈርቶች መቀመጣቸውን ገልፀዋል፡፡ በእዚህም መሰረት 40 በመቶ ፓርቲዎች በሚወዳደሩበት የፌደራል ወይም የክልል ምክር ቤቶች በሚያቀርቧቸው እጩዎች ብዛት የሚደለደል፣ 20 በመቶ በሚያቀርቧቸው የሴት እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት የሚደለደል፣ 10 በመቶ በሚያቀርቧቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት የሚደለደል መሆኑ ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡

በውይይቱ ላይ ለሴት እጩዎች ማቅረብ የተቀመጠው ቀመር በዝቷል የሚል ሀሳብ ከአንዳንድ ፓርቲዎች ተነስቶ የነበረ ሲሆን የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ መስፈርቶቹ የተቀመጡበትን ምክንያት አስረድተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ቀመሩን መሰረት በማድረግ ስለሚኖረው የአሰራር ስነስርዓት እና የግል ሚድያዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ላይ ለተሰነዘሩ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

# ፍርድ ቤቱ፣ ኢዜማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ያቀረበውን ክስ ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩን ምላሽ ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ

ህዳር 16 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ‹‹የመሰብሰብ ሕገ መንግሥታዊ መብታችን አይገደብ፤ ሁከት ይወገድልኝ›› በሚል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ያቀረበውን ክስ ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩን ምላሽ ለመስማት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ የፍትሐብሔር ችሎት ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን የፓርቲው ጠበቃ የሺዋስ አድማሱ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ኢዜማ በአዲስ አበባ ከተማ ተንሰራፍቷል ባለው ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ እና ኢ-ፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እደላን አስመልክቶ ያደረገውን ጥናት በጋዜጣዊ መግለጫ ለሕዝብ ለማድረስ ከራስ ሆቴል ጋር የከፍያና ተያያዥ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ ቢገኝም የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ መግለጫው በራስ ሆቴል እንዳይሰጥ ማገዱ ይታወሳል፡፡ መግለጫውን በራስ ሆቴል መስጠት ያልቻለው ኢዜማ፣ ለውስን ሚዲያዎች ብቻ በዋና ፅህፈት ቤቱ መግለጫውን መስጠቱ የሚታወስ ነው፡፡ መግለጫው በፓርቲው ፅህፈት ቤት ከተሰጠ በኋላም የመሬት ወረራና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኢ-ፍትሐዊ እደላ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም በፓርቲው ፅህፈት ቤት አዘጋጅቶት የነበረው የፓናል ውይይት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተፃፈ ደብዳቤ የተነሳ እንዳይካሄድ እገዳ እንደተደረገበት ፓርቲው ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡ ውይይቱ በተያዘለት እቅድ መሰረት አለመካሄዱን ተከትሎና በሕገ መንግሥቱ ላይ የሰፈረውን ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ነጻነትንና የመሰብሰብን መብት የሚጋፋ በመሆኑ ኢዜማ የከተማ አስተዳደሩ ላይ በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጥሪያው ማህተም የለውም በሚል መጥሪያውን ሳይቀበል ቀርቶ የነበረ ሲሆን ሕዳር 07 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የከተማ አስተዳደሩ በተወካዮቹ በኩል ቀርቦ መጥሪያውን ያልተቀበለው ማህተም ስላልተደረገበት እንደሆነ በማስረዳት በቀረበበት ክስ ላይ ምላሽ ይዞ ለመቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠው ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ ፍትሐብሔር ችሎትም የከተማ አስተዳደሩ ምላሹን ይዞ እንዲቀርብ ለሕዳር 22 ቀን 2013 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡